የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፵፰
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

18th Year No. 48
ADDIS ABABA 27th July, 2012

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፯፻፶፭/፪ሺ፬ ዓ.ም

ለስኳር ኢንዱስትሪ ልማት ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከሕንድ የኤክስፖርት ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ …… ገጽ ፮ሺ፫፻፸፬

CONTENTS

**Proclamation No.755/2012**

Export-Import Bank of India Credit Line Agreement to Provide Additional Loan for Financing Projects for the Development of Sugar Industry Ratification Proclamation. …….Page 6374

## አዋጅ ቁጥር ፯፻፶፭/፪ሺ፬

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሕንድ የኤክስፖርት ኢምፖርት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለስኳር ኢንዱስትሪ ልማት ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ፵፯ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (አርባ ሰባት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሕንድ የኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል እ.አ.አ ኤፕሪል ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፪ በኒውዴልሂ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION No. 755/2012.

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT LINE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE EXPORT-IMPORT BANK OF INDIA**

WHEREAS, a Credit Line Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export-Import Bank of India stipulating that the Export-Import Bank of India provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia additional credit amounting to 47,000,000 USD (Forty Seven Million United States Dollars) for financing projects for the development of sugar industry was signed in New Delhi on the 12th day of April 2012;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Credit Agreement at its session held on the 28th day of June 2012;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-article (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለስኳር ኢንዱስትሪ ልማት ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከሕንድ የኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፶፭/፪ሺ፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሕንድ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል እ.ኤ.አ ኤፕሪል ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፪ በኒውዴልሂ ከተማ የተፈረመው የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

፫. **የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፵፯ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (አርባ ሰባት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በስራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

፬. **አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፳ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም**

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Export Import Bank of India Credit Line Agreement to Provide Additional Loan for Financing Projects for the Development of Sugar Industry Ratification Proclamation No.755/2012".

2. **Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement signed in New Delhi on the 12th day of April 2012 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export-Import Bank of India is hereby ratified.

3. **Power of the Ministry of Finance and Economic Development**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for utilization of the Loan amount of 47,000,000 USD (Forty Seven Million United States Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. **Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 27th day of July, 2012.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**